# ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም እና የእግረ መስቀሉ ጉዞ



ከሊቀ ካህናት ዶ/ር መርዓዊ ተበጀ

# ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምና የእገረ መስቀል ጉዞ

ማውጫ — ገጽ

መግቢያ----------------------------------------I

ምዕራፍ ፩

የተሳላሚ ጉዞ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም-------------------5
ክፍል ፩ ኢየሩሳሌምና አካባቢዋ ---------------------------10
ክፍል ፪ ምሥራቅ እስራኤል------------------------------37
ክፍል ፫ ሰሜን እስራኤል---------------------------------43
ክፍል ፬ ሰሜናዊው እስራኤልና መካከለኛው ባሕር-----------58
ክፍል ፭ ምዕራብ እስራኤል-------------------------------63

ምዕራፍ ፪

የመስቀል ጦርነት ከየት ወደ የት-------------------------67

ምዕራፍ ፫

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ዓለም
አቀፍ ክርስቲያናዊ የአንድነት ንቅናቄ 60ኛ ዓመት
መታሰቢያ-------------------------------------------87

አባሪ
የተሳላሚ ጉዞ መርሃ ግብር ፳፻ ዓ.ም./2008----------- 103

# *ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምና የእግረ መስቀል ጉዞ*

## *መግቢያ*

ወደ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ስለሚደረገው የእግረ መስቀል ጉዞ ሁልጊዜ መሪ ሀሳብ ሁኖ የሚጠቀሰው በዳዊት መዝሙር ፻፳፩ በቁጥር ፩-፪ „ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሂድ ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ። ኢየሩሳሌም ሆይ እግሮቻችን በአደባባይሽ ቆሙ።“ የሚለው የምሥራች አብሣሪ የሆነው ዓረፍተ ነገር ነው። ቤተ እግዚአብሔርና ኢየሩሳሌም የሚለው ዓረፍተ ነገር በአይሁዶችም ሆነ በክርስቲያኖች ዘንድ የልብ ትርታ ሁኖ መኖሩን ምንጊዜም መረዳት ይቻላል። እንግዲህ ወደ እግዚአብሔር ቤት ከመሄድና በኢየሩሳሌም አደባባዮች ከመቆም የበለጠ ነገር ባለመኖሩ የተሳላሚ ጉዞ የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ከገነባው ከንጉሥ ሰሎሞንና ከንግሥተ ሳባ ጀምሮ ሳይቋረጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደ ጅረት ውኃ እየፈሰሰ ከዘመናችን ደርሷል። ወላጆቻችን ለዚህ የተሳላሚ ጉዞ የሠውት ጊዜያቸውንና ገንዘባቸውን ብቻ ሳይሆን ውድ ሕይዎታቸውን ጭምር እንደሆነ ከልብ መገንዘብ ይገባል። በገድላትና በድርሳናት ከተጻፈው ደመና ጠቅሶ፤ በመንፈስ ሠረገላ ተጭኖ፤ ኢየሩሳሌም ደርሶ ጎልጎታንና ቤተ ልሔምን ተሳልሞ፤ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ወይም በእግረ ኀሊና በሚደረገው ጉዞ ቅዱሳት መካናትን ተሳልሞ ከመመለስ አንጻር ያለውን ሁኔታ ለቅዱሳኑ ትተን፡፡ ሰው ሰውኛውን ብንመለከተው ወላጆቻችን በዘመናት መካከል የከፈሉትን መሥዋዕት በቃላት ገልጾ፤ በብዕር ቀርጾ ማስቀመጥ ያስቸግራል። እንኳን በዚያ አስቸጋሪ ክፍለ ዘመን ይቅርና አሁንም ዓለም „እንደ አንድ መንደር“ በሚታይበት ጊዜ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ቀላል አይደለም።

በዘመናት መካከል ወላጆቻችን የሱዳንንና የግብጽን በረሃ አቋርጠው፤ ገዳመ ቁስቋምን ተሳልመው፤ እስክንድርያን ጎብኝተው፤ ኢየሩሳሌም የደረሱ፤ ገዳም የመሠረቱ፤ ውርስ ያቆዩ ቢኖሩም፤ አብዛኞቹ ግን በአረቦችና በቱርኮች እጅ እየወደቁ ተዘርፈዋል፤ ተግድለዋል፤ በወጣትነት ዕድሜ ያሉት ደግሞ ባሪያ ሁነው ተሸጠዋል። በሱዳንና በግብጽ በረሃ ወድቀው የቀሩትን፤ አፋኝት የነደፋቸውን፤ አውሬ የበላቸውን፤ ውኃ ጥምና ረሀብ የፈጃቸውን ደግሞ ቤት ይቁጠረው። *„ስለ ጽድቅ የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፤ ይጠግባሉና።“* የሚለውን

መለኮታዊ መመሪያ አንገበው ስለተነሡ ሁሉንም ስለ ጽድቅ ሲሉ በደስታ ሲቀበሉት ኑረዋል። ስለሆነም ከዘመናችን ደርሷል። አሁንም የወላጆቻችንን አሠረ ፍኖት አንተውም በማለት የሱዳንንና የግብጽን በረሃ አቋርጠው በሲና ተራራ አድርገው ወደ ኢየሩሳሌም የሚገቡ መናንያን እንዳሉ የታወቀ ነው። ከተቻለ ሊበረታታ የሚገባው የተሳላሚ ጉዞ ነው።

በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ ቅድስት ሀገር ወደ ኢየሩሳሌም ስለሚደረገው የተሳላሚ ጉዞ የራሱ የሆነ ነባራዊ ባህል ነበረው። በመላው ኢትዮጵያ የሚገኙ ተሳላሚዎች ሁሉ የጥምቀትን በዓል በየቦታቸው ከአከበሩ በኋላ ሳይውሉ ሳያድሩ ጉዟቸውን ወደ ሀማሴን ያደርጋሉ። ዱባሩዋ በተባለውም ቦታ ይሰባሰባሉ። ይህ ቦታ የተወቀ የተሳላሚዎች መናሃሪያ መሆኑ ነው። በዚያም ጥቂት ቀናት እንደቆዩ፤ ተሳላሚው ሁሉ ከመላው ኢትዮጵያ ከቶ ከገባ በኋላ ጉዞው ይቀጥላል። ቢያንስ ከአንድ ሺህ ያላነሰ ተሳላሚ ከሀማሴን ተነሥቶ ይጓዛል። ከተሳላሚዎቹም መካከል ካህናትና መሳፍንት፤ ምእመናንና ምእመናት፤ መነኮሳትና መነኮስያት ይገኙባቸው ነበር። በመንገዱ ሁሉ ምዕራፈ ቅዱሳን እየተደረገ፤ ጸሎተ ማርያም እየተደገመ፤ ጸሎትና ምህላ እየተደረሰ፤ መዝሙር እየተዘመረ፤ ነጋሪት እየተጎሰመ፤ ሰንደቅ ዓላማው እየተውለበለበ፤ ብርቱው ደካማውን እያበረታታ የተሳላሚው ጉዞ ይቀጥላል። በጉዟቸውም ላይ የሚጸልዩት ጸሎትና የሚዘምሩት መዝሙረ ዳዊት ፻፳ ነበር። በዚህ መዝሙር ላይ የሚያተኩሩትም ነቢዩ ዳዊት ስለመንገደኛ የጸለየው ብሎም የዘመረው በመሆኑ ነው። እኛም ልብ ብለን ልንመለከተው፤ ልንጸልየውና ልንዘምረው ይገባል።

ከዚህ ላይ በዘመናት መካከል የተፈጸመውን ድርጊት በዚህ መግቢያ ላይ መግለጽ ተገቢ መስሎ ስለ ታየኝ እንደ ሚከተለው ቀርቧል። ዘመኑ በግልጽ ባይታወቅም የቱርክ ኦስማን መንግሥት ግብጽንና ሱዳንን፤ አረብያንንና መከከለኛውን ምሥራቅ አጠቃሎ ከያዘ እ.አ.አ. ከ1517 ዓ. ም. በኋላ ሳይሆን አይቀርም፤ ባሻ ሳሊም ግብጽን ድል አድርጎ ካይሮን በያዘበት ዘመን አባ አሥራተ ክርስቶስ የተባሉ ቆራጥ መናኝ መነኩሴ ከ1 500 በላይ የሚሆኑ ተሳላሚዎችን ይዘው ከላይ ከጠቀስነው ከሀማሴን ክፍለ ሀገር በመነሣት የተሳላሚ ጉዟቸውን ቀጠሉ። በሰላምም ኢየሩሳሌም ደርሰው፤ ቅዱሳት መካናትን ተሳልመው ወደ አገራቸው ሲመለሱ በባሻ ሳሊም ወታደሮች እጅ ወደቁ። በግፍ ተደበደቡ፤ ወደ በረሃ ተጣሉ፤ በዚያም ውስጥ በውኃ ጥምና በረሃብ አለቁ። የተረፉትም በባርነት ተሸጡ።

የዐባይን ምንጭ ለማሰስ በጎንደር ዘመነ መንግሥት ወደ ኢትዮጵያ የመጣው የእስኮትላንዱ ተወላጅ ጀምስ ብሩስ እንደመዘገበው ደግሞ በ1525 ዓ. ም. እንደገና 336 የኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች ሀማሴን ላይ ተሰበሰቡ። ከነዚህም መካከል ካህናትና መነኮሳት፤ 15ቱ ግን ሴት መነኮሳያት ነበሩ። ለ12 ቀናት በሰላም ከተጓዙ በኋላ በሽፍቶች እጅ ወደቁ። ከስንቃቸው ጀምሮ ያለ ሀብታቸውን ሁሉ ተዘረፉ። እንደ ምርኮኛ ተያዙ፤ ሽማግሌዎቹ ተገደሉ። ወጣቶቹ እንደ ባሪያ ተሸጡ። ከ336 ሰዎች መካከል 15ቱ ለጊዜው ሲያመልጡ በሕይወት ኢየሩሳሌም የደረሱት ሦስት ሰዎች ብቻ ነበሩ።

የዚህ ዓይነት ድርጊት ደግሞ በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት (1500-1532/ 1508-1540) ኢየሩሳሌም ላይ በአሰቃቂ መልኩ ተፈጽሟል። ከዚህ ላይ በአገር ውስጥ የግራኝ መሐመድ ወረራ እንዳለ ሁኖ፤ በውጭ በሚገኙ ኢትዮጵያውያን ላይ ደግሞ የቱርኮች እጅ እጅግ ከብዶ ነበር። ለአገር ውስጥ ታሪክ ብዙ ትኩረት የማይሰጠው ስንክሳር እንኳን ግንቦት ፲፩ ቀን በሚነበበው ክፍል ይህን የተሳላሚ ድርጊት በትንሹ መዝግቦት እናገኘዋለን። እንዲህም ይላል፤ „ ወበዛቲ ዕለት ኮነ ሰማዕተ አባ አሴር መምህረ ባሌ፤ ወዝንቱ ወሪዶ ውስተ ኢየሩሳሌም በዘመነ መንግሥቱ ለንጉሥ ወናግ ሰገድ ቅድመ መተሩ ክሣዶ በሰይፍ፤ ወድኅረ አውዓይዎ በእሳት በአንቀጸ ኢየሩሳሌም ኀበ ቆመ እግረ እግዚእነ። በረከቱ ተሀሉ ምስሌነ ለዓለም ዓለም አሜን።“ ወደ አማርኛ ሲመለስ „ በዚች ቀን የባሌ መምህር አባ አሴር በሰማዕትነት አረፈ። ይኸውም በንጉሥ ወናግ ሰገድ ዘመን ወደ ኢየሩሳሌም ወርዶ ሳለ መጀመሪያ አንገቱን በሰይፍ ቆረጡት። በኋላም የጌታችን እግር በቆመበት በኢየሩሳሌም መግቢያ በእሳት አቃጠሉት። በረከቱ ከእኛ ጋር ለዘለዓለም ትኑር አሜን።“ ይህ የባሌ መምህር የአባ አሴር የሰማዕትነት ታሪክ በጽሑፍ ስለሰፈረ ልናገኘው ቻልን እንጂ በዘመናት መካከል በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም ተሳላሚዎች ወገኖቻችን ላይ ሲደርስ የኖረው ግፍና መከራ፤ ሰቆቃውና እንግልት ይህ ነው ተብሎ በቃላት ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም። አሁንም ገና ያልታተመ ወይም ያለተዘጋ በመሆኑ ብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ „ይግባኝ ለክርስቶስ“ በሚለው መጽሐፋቸው በኢየሩሳሌም በተለይም ስለ ዴር ሡልጣን ገዳማችን ይዞታ ያለውን ግብግብ ሲገልጹ ያቀረቧቸው አቤቱታዎች ጊዜውና መልኩ ብሎም አቀራረቡ ይለያይ

እንጂ የሰማዕትነቱ ምዕራፍ ገና ተዘጋ ማለት አይቻልም። ይህንንም ወደ ፊት እንመለከተዋለን።

መለልሶ ለመግለጽ እንደተሞከረው እኛ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወገኖቻችን ኤርትራውያንም ስለ ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌምና ስለ ቅዱሳት መካናት ያለን ትስስር እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ወላጆቻችን እንደ ልብ ወደ ኢየሩሳሌም ሂደ መሳለም ካለመቻላቸው የተነሣ በአካባቢያቸው ያሉትን ቦታዎች በቅዱሳት መካናት ስም ሰይመዋቸው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌም ያህል ደብረ ሲና፤ ደብረ ጽዮን፤ ቤተ ልሔም፤ ኤፍራታ፤ ደብረ ታቦር፤ ደብረ ዘይት፤ ናዝሬት ቀራንዮ፤ ወዘተ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው አገራችን ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር፤ ሕዝቧም የተሰፋ ሕዝብ፤ የእስራኤል ዘነፍስ ወራሽ መሆኑን ያመለክታል። ልብ ብሎ ለተመለከው ጌታ ከጠራቸው ከቤተ እስራኤል ውጭ ለዓለም ክርስቲያኖች ሁሉ የጥምቀት ምስክርነት ቅጽ ሁኖ የሚጠቀሰው የመጀመሪያው የውጭ ክርስቲያን ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ የተናገረው ,,*ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ*=" (የሐዋ.ሥራ ፰፤ ፴፯) የሚለው ነው። አሁንም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ስለ ምናምንና ሰለ ምናሳምን በዚህ በእሥራ ምዕት ዓመት ሚሌኒዩም የትንሣኤን በዓል በቅድስት ሀገር በኢየሩሳሌም በጎልጎታ ዴር ሡልጣን ለማክበር ተዘጋጅተናል። መርሃ ግብሩም ከዚህ አነሰተኛ ጽሑፍ ጋር አብሮ እንዲታተም ተደርጏል። ከተሳላሚ ጉዞ ጋር በቀጥታም ይሁን ወይም በተዘዋዋሪ መልክ ግንኙነት ያላቸው ፩ኛ ,,*የመሰቀል ጦርነት ከየት ወደ የት*" ፪ኛ ,,*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ የአንድነት ንቅናቄ*" በሚል ርእስ የተጻፉ መጣጥፎች አብረው እንዲታተሙ ተደርጏል። ዓላማውም የኢየሩሳሌሟ ቤተ ክርስቲያን የሁሉም እናት ስለሆነች ዓለም አቀፍ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታስቦ ነው፤

አገሮቻችን በኢየሩሳሌም አደባባዮች በጎልጎታና በዴር ሡልጣን፤ በደብረ ጽዮንና በጽርሐ ጽዮን፤ በደበረ ዘይትና በጌቴሴማኒ፤ በደብረ ታቦርና በደብረ ቀርሜሎስ እንዲቆሙ ላደረገ፤ በገሊላና በሰማርያ ባሉ ቅዱሳት መካናት እንዲመላለሱ ለፈቀደ ሕያው አምላካችን ክብርና ምስጋና ይሁን። ለዘለዓለሙ አሜን።

መርዓዊ ተበጀ

## ማሳሰቢያ

ውድ ወገኖቼ

ይህ አነስተኛ ጽሑፍ በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ለሚደረ
የተሳላሚ ጉዞ እንደመነሻ ሁኖ ሊያገለግል ይችላል የሚል እም
አለኝ። ወደ ፊትም በዚህ ያልተካተቱ ቅዱሳት መካናት እንዲካ
ለማድረግ ዕቅድ ተይዟል። ስለዚህ አስተያየት ያላች
አስተያየታችሁን ብትሰጡኝ አመሰግናለሁ። እኔም አስተያየ
እንድሰጥ ከፈቀዳችሁልኝ፤ ምንጊዜ የተሳላሚ ጉዞ ወደ ቅድስት ሀ
ኢየሩሳሌም የሚል ራእይ በተስፋ ሰንቃችሁ እንድትኖሩ፤ አንድ ቀ
በተግባር እንድትፈጽሙት አሳስባለሁ፤ እጸልይማለሁ።

መ ል ካ ም የ ተ ሳ ላ ሚ ጉ ዞ


አድራሻ፤

Dr. Merawi Tebege
Ueckeratherstr. 2
D-50739 Koeln, Germany
Tel.& Fax: 0049 (0) 222- 599 2623